


# ዓለም አቀፍ  የጸሎት ቀን - ለአደጋ ለተጋለጡ ልጆች

ከሰኔ 27- 28 2003 ዓ.ም

## አንድ ሆነን ስለ ልጆች እንማልድ

ኢየሱስ  በእርሱ የሚያምኑት ሁሉ በፍቅር አንድ ይሆኑ ዘንድ ዓለምም በእነርሱ አንድነት የተነካ የእግዚአብሔርን ፍቅር ያይ ዘንድ እንዲህ ሲል ጸለዩ፡-

> ***«ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ። ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላከኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ፤ . . .» (ዮሐ 17፡ 20 – 23)።***

እኛ ክርስቲያኖችም እንደ ግለሰብ እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ዘንድ ያስቀመጠውን አቅምና ጸጋ በመጠቀም በተለያየ ደረጃ ልናሳርፍ የምንችለውን የተፅዕኖ አድማስ ዘወር ብለን ስናስብ ለአደጋ ስለተጋለጡ ሕፃናት በአንድነት መጸለይና ለእነሱም መሥራት ትልቁ ኃላፊነታችን ሊሆን ይገባዋል፡፡ በሁሉም የዓለም ክፍሎች እንደሚታወቀዉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የልጆችን ሕይወት በበጎም ሆነ በጎ ባልሆነ መንገድ የሚነኩ ሰባት ማሕበረሰባዊ ዘርፎች አሉ፡፡ ስለሆነም ጸሎታችን እነዚህ ዘርፎች በልጆች ላይ የሚያደርሱትን የተፅዕኖ ባሕርይና እንዴትም እንደሚያደርሱ ከማገናዘብ አንፃር መቃኘት አስፈላጊ ነዉ፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

### *የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቤተሰብና የትምህርት ዕድል ናቸዉ፡-*

እነዚህ ሁለቱ በልጆች ሕይወት ላይ ያላቸዉ ተፅዕኖ ግዙፍ ነዉ፡፡ ድኅነትና የቤተሰብ መፈራረስ  ባሉበት ሁኔታ የልጆች ሕይወት በመከራ ውስጥ ይወድቃል፡፡  የቤተሰብ መፈራረስ የሰዎችን የደስታ ስሜት ስለሚያጠፋ ማሕበራዊ ሕይወትን ክፉኛ ይጎዳል፡፡ ድኅነት በነገሠበት ሁኔታ የትምህርት ዕድል አይኖርም፤ ትምህርት በሌለበት ደግሞ የድኅነትን አዙሪት መስበር አይቻልም፡፡

**ምሣሌ 1**

***በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በአንድነት እንጸልይ፡-***

በልጆች የሚተዳደሩ ቤተሰቦችና የቤተሰቦቻቸው የአንድነት ሕይወት እንዳይፈርስ የሚጥሩ ልጆች ሥነልቡናዊና ተግባራዊ እገዛ እንዲያገኙ፤

በአብዛኛዉ ለተለያዩ ብዝበዛዎችና ጥቃቶች ተጋላጭነት ባላቸዉ ሴቶች  የሚመሩ በአንድ ወላጅ  (በእናት ወይም በአባት) ብቻ የሚተዳደሩ ቤተሰቦች ከድኅነት አዙሪት የሚወጡበትን ድጋፍ እንዲያገኙ፤

የትምህርት ዕድል ለድሆች ሁሉ እንዲሰጥ፤

ልጆች፡- መንፈሳዊ፣ አካላዊ፣ ስሜታዊ ፍላጎታቸውን በሚደርስና ሁለንተናቸውን በሚገነባ (holistic) ትምህርት ተኮትኩተዉ እንዲያድጉ እንዲሁም የሕይወት ክህሎት የሚያዳብሩበትን ዕድል እንዲያገኙ፤

በትምህርቱ መስክ የተሰማሩ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር መንግሥት መርሆን በማስረፅ አርዓያዊ ተግባር በማከናወን መልካም ተፅዕኖ ማሳረፍ እንዲችሉ፤

**በማስተዋል ምላሽ እንስጥ፡-**

እስቲ በዙሪያችሁ ያለውን ማህበረሰባዊ ፍላጎቶች ተመልከቱ፡፡ . . . የእናንተን እገዛ የሚፈልጉ ቤተሰቦች በዙሪያችሁ አሉን? ራሳቸውን የማስተዳደር ኃላፊነት የወደቀባቸዉ ልጆች ይኖሩ ይሆንን? በትምህርታቸዉ የእናንተን እገዛ የሚፈልጉ ልጆችስ?

### *ሦስተኛውና አራተኛዉ ደግሞ የሥራ ስምሪትና  መንግሥትን የሚመለከቱ ናቸዉ፡-*

እነዚህ ሁለቱ የአንድን አገር ሕዝብ ተኪ (መጪ ትውልድ) ተስፋ ያከስማሉ ወይም ያለመልማሉ፡፡ በዓለም ዙሪያ ዕድሜያቸዉ ከ5 – 17 ዓመት የሆነ 218 ሚሊዮን ሕፃናት ለጉልበት ብዝበዛ ተዳርገዋል፡፡ በርካታ መንግሥታትና የሥራ መስኮች በሙስና፣ በሥነ ምግባር ዝቅጠትና በስስት መንፈስ የመዋጣቸዉ ጉዳይ ችግሩን እንዳባባሰዉ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

**መዝሙር 89፡ 14**

***በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በአንድነት እንጸልይ፡-***

ለችግርና መከራ የተጋለጡ ልጆችን በመርዳት እንዲሁም ልጆች በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ የተሻለ ሥፍራ ይኖራቸዉ ዘንድ ገንዘባቸውን ያፈሰሱ ባለሐብቶችን እግዚአብሔር እንዲባርካቸው፣ የእነሱንም አርዓያነት የሚከተሉ ሌሎች ባለሐብቶች እንዲነሱ፤

ባለሐብቶች ሁሉ ለችግርና መከራ የተጋለጡ ልጆችን ጩኸት እንዲያደምጡ፤ አድምጠውም ለተግባራዊ ምላሽ እንዲንቀሳቀሱ፤

በመንግሥት የፍትሕ ሥርዓት ውስጥ ጽድቅና ፍትሕ ይሰርፅ ዘንድ፤

በሥልጣን ላይ ያሉ መንግሥታት ቀና መንፈስና ልቡና ይኖሯቸዉ ዘንድ፤ ለተተኪዉ ትውልድና ገና ወደ ፊት ለሚወለዱት ሕፃናት ሕይወት መልካምነት  የሚበጀውን ሁሉ እንዲያከናውኑ፤

በ2015 (እኤአ) ተግባራዊ ይሆናል ተብሎ ለሚጠበቀዉ የሚሊኔየሙ የልማት ግብ አስመልክቶ የገቡትን ቃል ኪዳን ይጠብቁ ዘንድ፤

***በማስተዋል ምላሽ እንስጥ:-***

በአካባቢያችን ደረጃ ያለን የእርስ በርስ መዋደድ በሕብረተሰቡ ውስጥ ምን ዓይነት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል? በወረዳችን/በክፍለ ከተማችን መስተዳድር ደረጃስ? የሥራ መስክና አሠራራቸውን በተመለከተ በወረዳና በብሔራዊ ደረጃ ለሚገኙት ትንንሽና ታላላቅ ባለሐብቶች የምንሰጠዉ ምላሽ ምንድን ነዉ? ከእነሱ ጋር ግንኙነት የምንፈጥረውስ በምን ዘዴ ነዉ?

***አምስተኛዉና ስድስተኛዉ:- መገናኛ ብዙኃንና ሥነጥበባዊ የመዝናኛ ፕሮግራሞች ናቸዉ:-***

በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠርን በመሆናችን እኛም የፈጠራ ሰዎች ነን፡፡ የፈጠራ ሥራዎች ለአደጋ ከተጋለጡ ልጆች አንፃር በአግባቡ ከተጠቀምንባቸዉ ታላቅ የመቤዠት ኃይል አላቸዉ፡፡ አሳዛኙ ጉዳይ ግን በተቃራኒዉ ለአሳሳችና ለአጥፊ ተልዕኮ ሊውሉ መቻላቸዉ ነዉ፡፡ እንደሚታወቀዉ የኢነተርኔትና የማሕበራዊ መገናኛ ብዙሐን ቴክኒዮሎጂ ዕድገት የግንኙነት (ተግባቦት) ዘይቤዎቻችንን ፈጽሞ እየለወጠዉ ነዉ፡፡ ይህንን ዕድል መልካም ተፅዕኖ ለማሳረፍ መጠቀም ይገባናል፡፡ የበርካታ ልጆችን አደጋ ተጋላጭነት በመቀነስ በኩልም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡

**ዘፍጥረት ፤፡ 27**

***ስለዚህም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በአንድነት እንጸልይ:-***

በመገናኛ ብዙኃን ዙሪያ የሚሠሩ ሰዎች የሚያስተላልፏቸዉ ፕሮግራሞች ‹ሕይወት ሰጪ› እና በእግዚአብሔር መንግሥት መርሆ የተሞሉ እንዲሆኑ፤ ከዚህም የተነሣ ተደራሲዎቻቸዉ ላይ መለኮታዊ ርህራሔ አድሮባቸዉ በዚህ ወቅት በመላዉ ዓለም ለአደጋ ለተጋለጡ ልጆች በጎ ምላሽ ለመስጠት እንዲችሉ፤

የመጪውን ትውልድ አመለካከት በበጎ ለመቅረጽ ጥረት ለሚያደርጉት ሁሉ ጸጋ እንዲበዛላቸዉ፤

የክፉውን ሃሳብና የክፋት ሥራ በመሥራት ላይ የሚገኙት መገናኛ ብዙኃን ተግባራቸዉ እንዲጋለጥና የልጆችን ሕይወት ከጥቃት መከላከል ይቻል ዘንድ፤

ፈጠራዊ የሥነ ጥበብና የመዝናኛ ሥራዎች ልጆች ከእግዚአብሔር የተሰጣቸውን ማንነት እንዲገልጹበት በማድረግ ለእግዚአብሔር ክብር ይውል ዘንድ፤

ለአደጋ ተጋላጭ ከሆኑ ልጆች ጋር የሚሠሩ የሥነ ጥበብ ሰዎች ልጆችን ከጉስቁልናና ከጥቃት የሚታደጉበት መለኮታዊ ሃሳብና የአሠራር ስልት እንዲፈልቅላቸዉ፤

**በማስተዋል ምላሽ እንስጥ:-**

መገናኛ ብዙሐን፣ ሥነ ጥበባዊ መዝናኛዎች:- በእኛም ሆነ በልጆቻችን ሕይወት ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንደሚያሳድሩ እናውቅ ይሆን? ተፅዕኖዎቹስ ሙሉ በሙሉ አዎንታዊ ናቸውን?

ለዜናነት ከበቁትና ከልጆች ጋር ከተያያዙ ወሬዎች መካከል በሕይወታችን ወይም በሕብረተሰባችን ዘንድ ምን መልካም ነገር አስደመጡን? የአካባቢ መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም መልካም ዜና ለሕብረተሰቡ እንዴት ማስተላለፍ  እንችላለን? የፈጠራ ሥራዎቻችንን እንዴት እንገልፃቸዋልን? ሌሎችን በተለይም ልጆችን በማበረታታት ረገድ እንዴት ልንጠቀምባቸዉ እንችላለን?

***ሰባተኛዉ ነጥብ የኃይማኖት ጉዳይ ነዉ:-***

ቤተክርስቲያን ተፅዕኖ የማሳረፍ ያላት ዕድል ታላቅ ነዉ፡፡ ቤተክርስቲያን የኢየሱስ ክርስቶስን እውነት፣ ተምሳሌታዊነት፣ እንዲሁም በፍቅሩ አንድ ሆነን በመሥራታችን የሚገለጠውን የመለወጥ ኃይሉን  የምናሳይባት መድረክ ነች፡፡ በኤድስ ክፉኛ በተጠቁት የምሥራቅና ደቡባዊ አፍሪካ አገሮች ቢያንስ 250,000 ቤተክርስቲያናት/ማሕበረ ምዕመናን አሉ፡፡ ይህም  12 ሚሊዮን ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆችን ለመርዳት ከበቂ በላይ የሆነ ኃይል ነዉ፡፡

**ያዕቆብ ፤፡ 27**

***ስለዚህም በሚከተሉት ነጥቦች ላይ በአንድነት እንጸልይ:***

ክርስቲያኖች ለአደጋ በተጋለጡ ላይ የሚደርሰውን ኢፍታሐዊ ድርጊት ለመናገር ሲጠየቁ ዋጋ ያለዉ ድምፃቸውን ለማሰማት የተዘጋጁ እንዲሆኑ፤

አጥቢያ ቤተክርስቲያናት በየአካባቢያቸዉ ማሕበረሰብ ዘንድ በተለይም በየደጃቸዉ ተጥለዉ ለሚገኙ ልጆች ፍላጎቶች  ምላሽ በመስጠት ረገድ የክርስቶስን ፍቅር ማንፀባረቅ እንዲችሉ፤

ቤተክርስቲያናት እግዚአብሔር እንደሚፈልገዉ መጠን ልጆችን ማገልገል የሚያስችላቸዉ አንድ ልብና መንፈስ እንዲኖራቸዉ፤

ልጆች የእግዚአብሔር ፍቅር መገለጫና  ራሳቸውም መልካም መሪ ሆነዉ ያድጉ ዘንድ ልጆች ከአዋቂዎች ጋር የክርስቶስ ወንጌል ሥራ ተካፋይ እንዲሆኑ፤

***በማስተዋል ምላሽ እንስጥ:-***

ከሌላ እምነት ተከታዮች ጋር አብሮ በመኖር ሂደት ለሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ምላሽ የምንሰጠዉ እንዴት ነዉ? ዘርፈ ብዙ የሆነውን የልጆችን ፍላጎት ለመድረስ ስንሻ «ራሳችንን በትህትና ዝቅ ባደረግን ልክ በውስጣችን ተስፋችንም ከፍ እንደሚል እርግጠኝነት ሊሰማን ይገባል፡፡ የእግዚአብሔር ክብር በሕይወታችን በመገለጡ ዓለም የእግዚአብሔርን ፍቅር እንደሚያይ ኢየሱስ በዮሐንስ 17 የጸለየዉ ጸሎት በተስፋ የተሞላ እንደ ነበር ልብ እንበል፡፡ እንግዲህ በጌታ ሞገስ ታጅበን፣ ለአደጋ የተጋለጡ ልጆችን በትህትናና በማገልገል  ወደ ታላቅ ክብሩ ለመድረስ የእኛ ፈንታ ነዉ፡፡